**ለአዘጋጁ**

**ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢ.ዜ.አ)**

**ከ ታይስ በርማን- የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ዋና ታዛቢ**

አዲስ አበባ ፣ ግንቦት 18 ቀን 2002 ዓ.ም.

ውድ አዘጋጅ ፡-

በኢትዮጵያ ግንቦት 15 የተካሄደውን ምርጫ የታዘበውን የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ያወጣውን ውጤት አስመልክቶ ዛሬ ጠዋት በኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ ላይ የወጣውንና «የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ብቁ፣ ብሄራዊ ምርጫውን ለማስፋፀም ሞያዊ ብቃት ያለው ነው አለ» በሚል የወጣውን ፅሁፍዎትን አንብቤዋለሁ፡፡ ዋና ታዛቢ እንደመሆኔ የኢትዮጵያ ህዝብ እኛ ያወጣነውን ውጤት በተመለከተ ትክክለኛ መረጃ የማግኘትን አስፈላጊነት እንደማምንበት ይገምታሉ፡፡

ቀደም ሲል ጋዜጠኛ እንደነበረ ሰው 11 ገጾች ብቻ ካለው ሪፖርታችን በአንድ አጭር ዘገባ ሁሉንም ነገር ማካተት እንደማይችሉ እረዳለሁ፡፡ ይሁንና ግን በዚህ ፅሁፍ ያካተቱት ስለምርጫው የተናገርናቸውን መልካም ነገሮችን ብቻ ነው፡፡ አንዳንድ መለስተኛ ቅሬታ ያቀረብንባቸውን ጥቃቅን ጉዳዮችን እንኳን በሚያሳዝን ሁኔታ አላካተቷቸውም፡፡

ዋናውን የምርጫ ሂደት በተወሰነ መልኩ አሳይተናል፡፡ በአንድ መልኩ ምርጫዎቹ በእለቱና ከዚያም በኋላ በጣም የተደራጁ፣የተቀናጁ፣ ሰላማዊ፣ የተረጋጉ ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለገዥውና ለተቃዋሚዎች የነበረው የፖለቲካ መወዳደሪያ ሜዳ ተመጣጣኝ አልነበረም፡፡ ገዥው ፓርቲ ለምርጫ ቅስቀሳው የመንግስትን ሀብት ተጠቅሞአል፡፡ በርካታ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ተሰደዋል አሊያም በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የግልፅነት ጉዳይ ሲነሳም አሳሳቢ ነው - እንደ መረጃ የማግኘት መብት ያሉ መሰረታዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ አልተከበሩም፡፡ እነዚህ ውጤቶቻችን በመረጃ የተደገፉና ከ170 በሚልቁት ብቃት ያላቸው ታዛቢዎቻችን ተይዘዋል፡፡

ልክ እንደእኔ እምነት የእርስዎም ጋዜጣም ለሚዛናዊ ዘገባ ተገቢውን ቦታ ይሰጣል የሚል ተስፋ አለኝ ይህንንም ለኢትየጵያ ህዝብ ማሳወቅ የሚፈልጉ ይመስለኛል፡፡ ይህንን ማድረግዎ በሚያሳዝን መልኩ የእርስዎ ዘገባ በጣሰው የኢትዮጵያ የምርጫ የስነምግባር መመሪያ (አንቀፅ 2.1፣ 2.2 እና 2.1ለ፣በረቂቁ አንቀፅ 3.1፣ 3.5) መሰረት አንባቢዎችዎ ባወጣነው ሪፖርት ላይ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የራሳቸውን አመለካከት እንዲይዙ ስለሚረዳ ነው፡፡

ምናልባትም የልዑኩን የማጠቃለያ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ በጋዜጣዎት ላይ ማተም ይጠይቅዎት ይሆናል፡፡ በዚህ ምትክ የምጠይቅዎት ይህንን ደብዳቤ ከጋዜጣዊ መግለጫችንና የዌብሳይታችንን መጠቆሚያ አንድ ላይ አድርገው (www.eueom-ethiopia.org) አንባቢዎችዎ የኛን መረጃዎች በአግባቡ እንዲጠቀሙ እንዲያደርጉልኝ ነው፡፡

ከሰላምታ ጋር

ታይስ በርማን

የአውሮፓ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ዋና ታዛቢ